This VIS translation is out of date. When you give your patient this translation, also give them the up-to-date English version of it.
To get both, and to find out what was updated, go to www.immunize.org/vis

**የክትባት መረጃ መግለጫ**
**VACCINE INFORMATION STATEMENT - AMHARIC**

# የኢንፍሉዌንዛ ክትባት
# Influenza Vaccine
## *እርስዎ ማወቅ የሚያስፈልግዎት*

(የጉንፋን ክትባት፣ በሕይወት ያለ፣ በአፍንጫ የሚሰጥ)

**2014-2015**

በርካታ የክትባት መረጃ መግለጫዎች በስፓኒሽና በሌሎች ቋንቋዎች ይገኛሉ። www.immunize.org/vis ይመልከቱ።

## 1 መከተብ ለምን ያስፈልጋል?

ኢንፍሉዌንዛ (“ጉንፋን”) በአሜሪካ በየክረምቱ፣ በተለይም በጥቅምትና ግንቦት መካከል የሚስፋፋ ተላላፊ በሽታ ነው።

ጉንፋን የሚመጣው በኢንፍሉዌንዛ ቫይረሶች ሲሆን፣ በሳል፣ በማስነጠስ እና በንክኪ ሊተላለፍ ይችላል።

ማንኛውም ሰው ጉንፋን ሊይዘው ይችላል። ነገር ግን በጉንፋን የመያዝ አደጋ በልጆች ላይ ከፍተኛ ነው። ምልክቶቹ በድንገት ሊጀምሩና ለበርካታ ቀናት ሊቆዩ ይችላሉ። እነዚህም የሚከተሉትን ያካትታሉ፦

- ትኩሳት/ብርድ ብርድ ማለት
- የጉሮሮ መቁሰል
- የጡንቻ ህመም
- ድካም
- ሳል
- ራስ ምታት
- ንፍጥ ወይም የአፍንጫ መደፈን

ጉንፋን አንዳንድ ሰዎችን ከሌሎች በበለጠ ሊያሳምማቸው ይችላል። እነዚህም ልጆች፣ 65 ዓመትና ከዚያ በላይ የሆናቸው ትልልቅ ሰዎች፣ እርጉዝ ሴቶች፣ እና የተወሰኑ የጤና እክል ያለባቸው ሰዎች - ለምሳሌ የልብ፣ የሳንባ ወይም የኩላሊት በሽታ፣ የነርቭ ስርዓት በሽታ ወይም የተዳከመ በሽታ የመከላከል አቅም ያላቸው ሰዎች ናቸው። የጉንፋን ክትባት በተለይ ለእነዚህ ሰዎችና ከእነርሱ ጋር ንክኪ ላለው ሰው ጠቃሚ ነው።

ጉንፋን ወደ ኒሞኒያ ሊቀየር እና ያሉትን የጤና ችግሮች እንዲባባሱ ሊያደርግ ይችላል። በልጆች ላይ ተቅማጥና ከቁጥጥር ውጪ የሆነ መንቀጥቀጥ ሊያስከትል ይችላል።

በየአመቱ **በአሜሪካ ውስጥ በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች በጉንፋን ይሞታሉ፣** እንዲሁም በርካቶች ሆስፒታል ይገባሉ።

**የጉንፋን ክትባት** ጉንፋንን እና የሚያስከትላቸውን የተወሳሰቡ ችግሮች ለመከላከል የተሻለ መንገድ ነው። የጉንፋን ክትባት ጉንፋን ከሰው ወደ ሰው እንዳይተላለፍም ይከላከላል።

## 2 ሕይወት ያለው፣ የተዳከመ የጉንፋን ክትባት - LAIV፣ አፍንጫ ውስጥ የሚነፋ

አሁን የሚወስዱት live, attenuated influenza vaccine - **በሕይወት ያለ፣ የተዳከመ የኢንፍሉዌንዛ ክትባት** (LAIV በመባል ይታወቃል) አፍንጫ ውስጥ የሚነፋ ክትባት ነው። “Attenuated” ማለት “የተዳከመ” ማለት ነው። በክትባቱ ውስጥ ያሉ ቫይረሶች የተዳከሙ ስለሆኑ ሊያሳምሙዎ አይችሉም።

ሌሎች “ኢንአክቲቬትድ” እና “ሪከምቢናንት” በሕይወት ያለ ቫይረስ የሌላቸው የጉንፋን ክትባቶች አሉ። እነዚህ “የጉንፋን ክትባቶች” በመርፌ የሚሰጡ ናቸው።

*በመርፌ የሚሰጡ የጉንፋን ክትባቶች መረጃ በሌላ መግለጫ ተገልጿል።*

የጉንፋን ክትባት በየአመቱ እንዲወሰድ ይመከራል። አንዳንድ ከ6 ወር እስከ 8 ዓመት ያሉ ልጆች በአመት ሁለት መጠን መውሰድ ሊያስፈልጋቸው ይችላል።

የጉንፋን ቫይረሶች ሁልጊዜ ይቀያየራሉ። በየአመቱ የጉንፋን ክትባት የሚሰራው በዚያ ዓመት ጉንፋን ሊያስከትሉ ይችላሉ ተብለው የታመነባቸውን ቫይረሶች እንዲከላከል ተደርጎ ነው። LAIV ከ4 የተለያዩ ቫይረሶች የሚከላከል ነው። የጉንፋን ክትባት ሁሉንም የጉንፋን አይነቶች አይከላከልም ይሁን እንጂ በሽታውን ለመከላከል የተሻለ መንገድ ነው።

ከክትባት በኋላ የመከላከል አቅም እስኪጎለብት ድረስ 2 ሳምንት ይወስዳል፣ እንዲሁም የመከላከል አቅሙ ከበርካታ ወራት እስከ አመት ድረስ ይዘልቃል።

አንዳንድ በኢንፍሉዌንዛ ቫይረስ የማይከሰቱ ሕመሞች በአብዛኛው ጉንፋን እንደሆኑ ተደርገው በስህተት ይወሰዳሉ። የጉንፋን ክትባት እነዚህን ሕመሞች አይከላከልም። ኢንፍሉዌንዛን ብቻ ነው የሚከላከለው።

LAIV **ከ2 እስከ 49 አመት ዕድሜ** ላሉ ሰዎች ሊሰጥ ይችላል። ከሌሎች ክትባቶች ጋር ያለችግር በተመሳሳይ ጊዜ ሊሰጥ ይችላል።

LAIV ቴሜሮሳል ወይም ሌላ ማቆያ ንጥረ ነገር የለውም።

## 3 አንዳንድ ሰዎች ይህንን ክትባት መከተብ የለባቸውም

ክትባቱን ለሚሰጥዎ ሰው ይህንን ያሳውቁ፦

- **በጣም አደገኛ የሆነና ለህይወት የሚያሰጋ የማይስማማዎት ነገር (አለርጂ) ካለብዎ፣** (ለምሳሌ) የጀላቲን ወይም የአንቲባዩቲክ አለመስማማትን ይጨምራል። የጉንፋን ክትባት ከተከተቡ በኋላ ለህይወት የሚያሰጋ አለመስማማት ገጥሞዎት የሚያውቅ ከሆነ፣ ወይም ለማንኛውም የዚህ ክትባት ክፍል አለርጂ ካለብዎ ክትባቱን መከተብ የለብዎትም።
- **Guillain-Barre Syndrome (በጣም አደገኛ የሆነ ሽባ የሚያደርግ በሽታ፣ ጂቢኤስ በመባልም ይጠራል)** ታመው የሚያውቁ ከሆነ። አንዳንድ ጂቢኤስ ታመው የሚያውቁ ሰዎች ይህንን ክትባት መከተብ የለባቸውም። ይህንን ከሐኪምዎ ጋር መነጋገር አለብዎ።
- ለ ረጅም ጊዜ የቆየ የጤና ችግር ካለብዎ፣ እንደ የተወሰነ የልብ፣ የአተነፋፈስ፣ የኩላሊት፣ የጉበት፣ ወይም የነርቭ ስርዓት ችግር ካለብዎ፣ ሐኪምዎ LAIV ክትባት መውሰድ መቻል አለመቻልዎን ለመወሰን ይረዳዎታል።

U.S. Department of Health and Human Services
Centers for Disease Control and Prevention

This VIS translation is out of date. When you give your patient this translation, also give them the up-to-date English version of it. To get both, and to find out what was updated, go to www.immunize.org/vis

- **ባለፉት 4 ሳምንታት ሌሎች ክትባቶች ወስደው ከሆነ ወይም ጤንነት ካልተሰማዎ።** በመጠኑ ታመው እያለ መከተብ ብዙ ጊዜ ችግር የለውም፣ ነገር ግን እስኪሻልዎ እንዲጠብቁ ሊጠየቁ ይችሉ ይሆናል። ሲሻልዎት ተመልሰው መምጣት አለብዎ።

- በአፍንጫ ከሚነፋው ክትባት ይልቅ በመርፌ የሚሰጥ የጉንፋን ክትባት መውሰድ አለብዎ እርስዎ፡-

  - እርጉዝ ከሆኑ
  - የተዳከመ የሰውነት በሽታ የመከላከል አቅም ካልዎት
  - እንቁላል የማይስማማዎት ከሆነ
  - አስም ወይም ስትተነፍስ ኩርኩር የማለት ችግር ያለብህ ትንሽ ልጅ ከሆንክ
  - ለረጅም ጊዜ አስፐሪን በመውሰድ ላይ ያለህ ልጅ ወይም ወጣት ከሆንክ
  - በ7 ቀን ጊዜ ውስጥ የተዳከመ የሰውነት በሽታ የመከላከል አቅም ያለው ሰው የሚንከባከቡ ወይም የሚጠይቁ ከሆነ
  - ባለፉት 48 ሰዓታት ውስጥ የጉንፋን መድሃኒቶች ወስደው ከነበረ

ክትባቱን የሚሰጥዎት ሰው ተጨማሪ መረጃ ሊሰጥዎት ይችላል።

## 4 የክትባቱ አለመስማማት አደጋዎች

ክትባት፣ እንደ ማንኛውም መድሃኒት፣ አላስፈላጊ ውጤቶች ሊታስከትል የሚችልበት እድል አለ። እነዚህ አብዛኛውን ጊዜ ቀላል እና በራሳቸው የሚድኑ ናቸው።

ከማንኛውም ክትባት በኋላ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮች፡-

- በክትባት የሚከሰት በጣም አደገኛ የሆነ የአለመስማማት ችግር የተለመደ አይደለም፣ በግምት ቢያጋጥም ከአንድ ሚሊዮን መጠኖች ከአንድ በአነሰ ላይ ነው። የሚያጋጥም ከሆነ ከክትባት በኋላ ከጥቂት ደቂቃዎች እስከ ጥቂት ሰዓታት ባለው ጊዜ ውስጥ ነው የሚከሰተው።

ከLAIV ክትባት በኋላ ሪፖርት የተደረጉ ቀላል ችግሮች፡-

*እድሜያቸው ከ2-17 በሆኑ ልጆችና ወጣቶች ላይ፡-*

- ንፍጥ፣ የአፍንጫ መታፈን ወይም ሳል
- ትኩሳት
- ራስ ምታትና የጡንቻ ሕመም
- በሚተነፍሱ ጊዜ የሳንባ ኩርኩር ማለት
- የሆድ ሕመም ወይም አልፎ አልፎ ማስታወክ ወይም ማስቀመጥ

*እድሜያቸው ከ18-49 በሆኑ ትልልቅ ሰዎች ላይ ፡-*

- ንፍጥ ወይም የአፍንጫ መታፈን
- የጉሮሮ መቁሰል
- ሳል፣ ብርድ ብርድ ማለት፣ ድካም/ሀይል ማጣት
- ራስ ምታት

LAIV የሚሰራው ከተዳከመ ቫይረስ ስለሆነ **ጉንፋን** አያስይዝም።

ልክ እንደ ማንኛውም መድሃኒት፣ ክትባት ከባድ የሆነ ጉዳት ወይም ሞት ሊያስከትል የሚችልበት በጣም አነስተኛ እድል አለ።

የክትባቶች ደህንነት ሁልጊዜ ቁጥጥር ይደረግበታል። ለተጨማሪ መርጃ፣ www.cdc.gov/vaccinesafety/ን ይመልከቱ።

## 5 ከባድ የሆነ አለመስማማት ካስከተለብኝስ?

### ምን መመልከት አለብኝ?

- የሚያሳስብዎትን ማንኛውንም ነገር ይመልከቱ፣ ለምሳሌ በጣም አደገኛ የአለመስማማት ምልክቶች፣ ከፍተኛ ትኩሳት፣ ወይም የባህርይ ለውጥ።

በጣም አደገኛ የአለመስማማት ምልክቶች እነዚህን ያካትታሉ የቆዳ መቆጣት፣ የጉሮሮ እና የፊት ማበጥ፣ የመተንፈስ ችግር፣ ፈጣን የልብ ትርታ፣ ራስ ማዞር እንዲሁም ድካም። እነዚህም ክትባቱን ከተከተቡ ከጥቂት ደቂቃዎች ወይም ሰዓታት በኋላ ሊጀምሩ ይችላሉ።

### ምን ማድረግ አለብኝ?

- በጣም አደገኛ የአለመስማማት ምልክት ወይም ሌላ ሊቆይ የማይችል አጣዳፊ ነገር ከመሰልዎት፣ 9-1-1 **ይደውሉና** የታመመውን ሰው ወደ አቅራቢያዎ ሆስፒታል ይውሰዱ። ይህ ካልሆነ ግን ወደ ሐኪምዎ ይደውሉ።

- በመቀጠልም፣ ችግሩ ለክትባት ተቃራኒ ክስተቶች ማሳወቂያ ዘዴ (VAERS) ሪፖርት ሊደረግ ይገባል። ሐኪምዎ ሪፖርት ሊያደርግልዎ ይችላል ወይም እርስዎ ራስዎ በVAERS ድረ ገጽ www.vaers.hhs.gov ላይ ወይም በ1-800-822-7967 በመደወል ማሳወቅ ይችላሉ።

*VAERS የህክምና ምክር አይሰጥም።*

## 6 ብሔራዊ የክትባት ጉዳት ካሳ መርሃ ግብር

ብሔራዊ የክትባት ጉዳት ካሳ መርሃ ግብር (VICP) በአንዳንድ ክትባቶች ምክንያት የተጎዱ ሰዎችን ለመካስ የተቋቋመ የፌደራል መርሃ ግብር ነው።

በክትባት ምክንያት ጉዳት ደርሶብናል ብለው የሚያምኑ ሰዎች ስለ መርሃ ግብሩ እና ቅሬታቸውን ስለማቅረብ ግንዛቤ ለማግኘት **በ1-800-338-2382** በመደወል ወይም የVICP ድረ ገጽ **www.hrsa.gov/vaccinecompensation** በመቃኘት መረዳት ይችላሉ። ካሳ ይገባኛል ብሎ ለመጠየቅ የጊዜ ገደብ አለው።

## 7 ተጨማሪ ግንዛቤ እንዴት ማግኘት እችላለሁ?

- ሐኪምዎን ይጠይቁ።
- ወደ አካባቢዎ ወይም ወደ ግዛቱ የጤና ክፍል ይደውሉ።
- ከበሽታ ቁጥጥር እና መከላከል (CDC) ማዕከላት ጋር ይገናኙ፡-
  - በስልክ ቁጥር 1-800-232-4636 (1-800-CDC-INFO) በመደወል፣ ወይም
  - የCDCን ድረ ገጽ www.cdc.gov/ftu ይመልከቱ።

የክትባት መረጃ መግለጫ (ጊዜያዊ)

**ሕይወት ያለው የተዳከመ የኢንፍሉዌንዛ ክትባት**

Office Use Only

08/19/2014

42 U.S.C. § 300aa-26



Translation provided by Swedish Hospital, Seattle, WA